# ደንብ

**ሞንትጎሞሪካውንቲፐብሊክስኩልስ**

ተዛማጅ ሠነዶች፦ DIA-RA, DIA-RB, ECK, ECK-RA, IQD, IQD-RA, IID-RB, JFA, JFA-RA, JGA
ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦ የትምህርት አመራር እና ማሻሻያ ዲቪዥን፣የመማር - ማስተማር ክፍል Division of School Leadership and Improvement; Division of Teaching and Learning

## ተጨማሪ የሥርአተ ትምህርት እና የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች

I. ዓላማ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ IQD *መሠረት ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች*ን ለመተግበር በትምህርት ቤት ደረጃ የአፈጻፀም ሂደት መመሥረት።

የስርአተ ትምህርት ተጉዳኝ እንቅስቃሴዎችን (ECAs) ከስርአተ ትምህርቱ (CCAs) የተለየ ተጉዳኝ መሆኑን ለመግለጽ

ለመካከለኛ ደረጃ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች CCAs እና ECAs የአካዳሚክ ብቁነት መስፈርት ሊኖራቸው የሚችልበትን ሁኔታ መመስረት።

II. የቀድሞው ዳራ

ቦርዱ ከመደበኛ ትምህርት ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ መደበኛ የትምህርት ክትትልን እና ተሳትፎን የሚያዳብር መሆኑን አረጋግጧል። ቦርዱ ከክፍል ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች በእኩዮች እና በጎልማሶች መካከል አወንታዊ መስተጋብርን እንደሚያዳብር ተመልክቷል፤ ለምሳሌ፦ በክለቦች፣ በፈጠራ ሥራዎች፣ እና በስነ ጥበባት ቡድኖች፣ እና በሙያዊ እና በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄዱ ስፖርቶች፣ ለተማሪዎች ስሜታዊ፣ ማህበራዊ፣ እና አእምሯዊ እድገት እና አጠቃላይ የትምህርት ስኬት ወሳኝ ግንኙነቶችን ለመገንባት አስፈላጊ ነው።

በመደበኛ ትምህርት ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ በአካዳሚክ ምዘና መደገፍ እንዳለበት ቦርዱ ቢገነዘብም፣ የአካዳሚክ ብቁነት መስፈርቶችን በተመለከተ የተማሪዎችን በትምህርት ቤት ቁልፍ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍን ማደናቀፍ እንደሌለበት ይገነዘባል።

III. ትርጉም

A. *ከመደበኛ ትምህርት ተጓዳኝ እንቅስቃሴ* (CCA) ማለት ከክፍል ውጪ፣ በክፍል ውስጥ ወይም በትምህርት ቀናት የሚካሄድ የትምህርት ኮርስ ተግባር/እንቅስቃሴ ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች መስፈርቶችን በማሟላት መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። CCAs ከክፍል ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን ለምሳሌ፦ የክፍል ተማሪዎች የመስክ ጉዞ ወይም "Lathrop E. Smith Environmental Education Center" የሚያካሄደውን የትምህርት መርሃ ግብር ያካትታል።

B. *ከመደበኛ ትምህርት ተጓዳኝ እንቅስቃሴ* (ECA) ማለት በተማሪዎች ፍላጎት ዙሪያ የተደራጀ እና MCPS ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች ክፍት የሆነ በፈቃደኝነት እና በተማሪዎች የሚመሩ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

C. *የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ንብረት* ማንኛውንም ትምህርት ቤት ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በባለቤትነት የተያዘ ወይም የሚተዳደር ግቢን ጨምሮ ሌላ የ MCPS ፋሲሊቲ፣ በ MCPS ባለቤትነት የተያዙ፣ የሚተዳደሩ ወይም በኮንትራት የሚሠሩ

አውቶቡሶች እና ሌሎች ተሽከርካሪዎች፤ እና ማንኛውም በ MCPS መርሃግብር ተማሪዎች የሚያሳትፉበት ንብረት እና ግቢ ማለት ነው። ተማሪዎች MCPS ንብረት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ ለሚከሰት ተቀባይነት የሌለው የባህሪ መዘዝ MCPS የተማሪ ስነምግባር ህግ ላይ የተቀመጠው የባህሪ ጣልቃገብነት ደንብ ተፈጻሚ ይደረጋል።

D. *በትምህርት ቤት የሚደገፉ* ECAs ፈቃድ የተሰጣቸው እና በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረጉ፣ ዳይሬክተሩ/ተወካይ (ለምሳሌ፦ ECA ዳይሬክተር) የፀደቁ ተግባራት። ትርጉሙ እንደሚያመለክተው፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚያካሄደው ECA የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ የሆነ እና ተማሪዎችን እና ሌሎች ተግባራትን በዚህ ደንብ እና በድርድር ስምምነቶች መሠረት የመቆጣጠር ሃላፊነት ያለው ሰው ስፖንሰር ሊኖረው ይገባል።

IV. ለተጨማሪ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች ብቁነት

A. ሁሉም ECAs በቦርድ ፖሊሲ ACA *መሠረት አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና ብቁ ባህል* የሠፈነበት እና ግልጽ በሆነ ትክክለኛ ወይም የሚታወቁ የግል ባህሪያት ላይ በመመስረት ያለ አድልዎ ለሁሉም ተማሪዎች ክፍት ይሆናሉ፣ይህም የሚከናወነው የተገለጹትን የእንቅስቃሴውን አላማዎች ለማሟላት አስፈላጊ በሆኑ መመዘኛዎች ብቻ ነው።

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ECAs ይሰጣሉ።

2. ተማሪዎች ወቅታዊ ፍላጎቶችን እና ዝንባሌዎችን በሚያረኩ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ እና ልምዶቻቸውን ለማስፋት የሚጠቅሙ እንቅስቃሴዎችን መቃኘት እንዳለባቸው ይበረታታሉ።

3. ርእሰ መምህራን ECAs ውስጥ በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ገደቦችን የማስቀመጥ ስልጣን ይኖራቸዋል–

a) የዲሲፐሊን ደንቦችን መጣስ፣ እና

b) እንቅስቃሴው በሚካሄድበት ቀን ያለምክንያት መቅረት።

B. አካዳሚያዊ ብቁነት

1. በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ለመሳተፍ ECAs የአካዳሚክ ብቁነት መስፈርት ማቋቋም አይችልም፦

a) የአካዳሚክ ብቁነት መስፈርቶች (ለምሳሌ፦ ናሽናል ኦነር ሶሳይቲ) ብሔራዊ፣ የስቴት ወይም የሪጅናል ድርጅቶች ተባባሪ ከሆነ ECAs ተዛማጅ ድርጅት መመዘኛዎች ጋር የሚጣጣሙ የአካዳሚክ ብቁነት መስፈርቶችን ሊያቋቁሙ ይችላሉ።

b) ለኢንተርኮላስቲክ አትሌቲክስ የብቃት መመዘኛዎች የአካዳሚክ ብቁነትን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ እና MCPS ደንብ IQD-RA *መሠረት በኢንተር ስኮላስቲክ አትሌቲክስ ውስጥ ለሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአካዳሚክ ብቁነት* እና MCPS ደንብ IQB-RA *መሠረት፣ ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአካዳሚክ ብቁነት፣ከተጨማሪ የእድሜ ብቃት ጋር በአትሌቲክስ ተካፋይ ስለመሆን* የጤና መስፈርቶች።

2. የአካዳሚክ ብቁነት መስፈርቶች እና በአጋር ድርጅት የተገለጹ ማናቸውም ተጨማሪ

መስፈርቶችን በቅድሚያ ማሳወቅ አለባቸው።

V. የአፈጻጸም ሒደት

A. ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች ፕሮግራም ማቋቋም

1. በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ ርእሰ መምህር/ተወካይ በትምህርት ቤት ECAs ላይ የመሳተፍ ወይም የመፍጠር እድሎችን ለተማሪዎች ማሳወቅ አለባቸው።

2. MCPS ደንብ JFA-RA፣ *የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች፣*ተማሪዎች እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች በበቂ ሁኔታ ፍላጎትን የሚያሟላ እና ድጋፍ የሚሰጥ እንዲሁም እንቅስቃሴው ከቦርድ ፖሊሲዎች ወይም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመሪያዎች (ከዚህ በኋላ "MCPS ደንቦች") ተብሎ የሚጠራው ደንብ የሚከበርበት ECA የማደራጀት ወይም የመምከር መብት አላቸው።

3. በት/ቤቱ ውስጥ የሚገኙ አጠቃላይ ECAs መርሃ ግብሮች ለሁሉም ተማሪዎች በቂ እና የተለያዩ እድሎችን የሚሰጡ ሁሉን አቀፍ እና ሚዛናዊ መሆን አለባቸው።

B.ፕሮግራሙን ማስተዳደር

1. ተማሪዎች ወቅታዊ ዝንባሌዎችን እና ፍላጎቶችን በሚያረኩ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ ወይም እንዲፈጥሩ እንዲሁም ፍላጎቶቻቸውን እና ልምዶቻቸውን ለማስፋት እንቅስቃሴዎችን እንዲመረምሩ ማበረታታት አለባቸው። አንዳንድ ተማሪዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲሳተፉ ማበረታቻ ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን፣ ECA ውስጥ ከመጠን ያለፈ መሳተፍን በተመለከተ ሌሎች ምክር ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

2. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን ECA ፕሮግራም መርሐግብር ይወስናል። ECAs ከትምህርት ቀን ውጭ እንዲሁም በትምህርት ቀን ሆኖ ትምህርት በማይሰጥበት ሠዓት ሊከናወኑ ይችላሉ። የተማሪዎች እንቅስቃሴ መርሃ ግብር በሚዘጋጅበት ጊዜ በአውቶቡስ የሚጓጓዙ ተማሪዎች ብዛት እና የእግረኛ ተማሪዎች ብዛት ቁጥር ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ብዙ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በአውቶቡስ የሚጓጓዙ ተማሪዎች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቀን አብዛኞቹን ECAs መርሐግብሮች ማስያዝ አስፈላጊ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ሌሎች ለምሳሌ:- በእግር ጉዞ ርቀት ያሉ ማህበረሰቦችን የሚያገለግሉ ትምህርት ቤቶች፣ ለጠቅላላ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ፕሮግራም ከትምህርት ሠዓት በኋላ ማካሄድ የሚሻል መሆኑን ሊወስኑ ይችላሉ።

3. ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ በትምህርት ቤት በሚደገፈው ECA ውስጥ ለመሳተፍ ለሚያስፈልጉ ወጪዎች (ለምሳሌ:- የተለየ ልብስ ወይም ቁሳቁስ) የእንቅስቃሴ ፈንድ በነጻ እንዲጠቀሙ መፍቀድ ይችላሉ። ማንኛውም ተማሪ ተስፋ እንዳይቆርጥ ወይም በወጪ ምክንያት እንዳይገለሉ ስፖንሰሮች እያንዳንዱን ትምህርት ቤት የሚደግፈውን ECA ወጪዎችን መቆጣጠር፣ መከታተል፣ እና እንደአግባቡ ገንዘብ ማፈላለግ አለባቸው።

4. በ IAF ፈንድ የሚደገፉ የ ECA ወጪዎች MCPS ደንብ DIA-RA፣ *ፋይናንሺያል ኦፕሬሽንስ/የተለየ እንቅስቃሴ ፈንድ ሂሳብ አያያዝ* በተመለከተ በተገለጸው አሰራር መሰረት መተዳደር አለባቸው።

C. የመደበኛ ትምህርት ተጓዳኝ እንቅስቃሴ ስፖንሰሮች

1. እያንዳንዱ በትምህርት ቤት የሚደገፍ ECA፤ MCPS ደንብ JFA-RA፣ *የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች* ድንጋጌ መሠረት እንደአግባቡ ከሚመለከታቸው ተማሪዎች ጋር በመመካከር በርእሰመምህሩ የተሰየመ(ች) እና በአካባቢው ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ፈቃድ የተሰጠ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ስፖንሰር ሊኖረው ይገባል።

   a) ECA ስፖንሰር ሚናው የእንቅስቃሴውን አጠቃላይ ሃላፊነት ለመወጣት እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ህግጋት በማክበር ርእሰመምህሩን መወከል ነው። ስፖንሰር አድራጊው(ዋ) በቡድኑ ወይም በቡድን አባላት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንቦች ከተጣሱ ለርእሰ መምህሩ/ዲዛይኑ ማሳወቅ አለበት።

   b) ECA ስፖንሰሮችን የመሰየም ክፍያዎች እና መስፈርቶችን በተመለከተ በድርድር ስምምነት ይፈፀማል።

2. ደንብ JFA-RA፣ *የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች* መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት፣ በትምህርት ቤት ያልተደገፉ በተማሪዎች-ተነሳሽነት የሚካሄዱ ክለቦች በትምህርት ቤት እንደሚደገፍ ክለብ ሊወከሉ ወይም በተመሳሳይ ሊታዩ አይችሉም።

   a) የትኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ እንደዚህ ዓይነት ስብሰባዎችን አይመራም ወይም ተሳታፊ አይሆንም/አትሆንም። ነገር ግን የ MCPS ሰራተኛ የደህንነት ክትትል ሊያደርግ ይችላል/ትችላለች።

   b) የትምህርት ቤት ባልደረባ ያልሆኑ ሰዎች የቡድን ስብሰባዎችን አይመሩም፣ አያካሄዱም፣ አይቆጣጠሩም፣ ወይም ስብሰባው ላይ በመደበኛነት መገኘት የለባቸውም።

   c) ትምህርት ቤት-ስፖንሰር ያላደረጋቸው የተማሪ ስብሰባዎችን እና ክለቦችን በተመለከተ ያሉትን ተጨማሪ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ደንብ JFA-RA ይመልከቱ።

D. የፕሮግራሙ ግምገማ

በየዓመቱ፣ ርእሰ መምህሩ/ተወካይ፣ ECA ስፖንሰሮች እና ተማሪዎች ጋር በመተባበር፣ ከቦርድ ፖሊሲ IQD፣ *ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች* ጋር ለማጣጣም ይህንን ደንብ፣ እና ስፖንሰር አድራጊዎችን የሚቆጣጠሩ በድርድር የተፈፀሙ ስምምነቶች ውስጥ ያሉትን ድንጋጌዎች እና ECA ፕሮግራሞችን ይገመግማል።

E. የተጓዳኝ-ሥርዓተ ትምህርት እንቅስቃሴ ድንጋጌዎች

1. የሥርዓተ ትምህርት ተጓዳኝ-እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከስርአተ ትምህርት ጋር በተያያዙ ኮርሶች ላይ የሚደረጉት የውጤት አሰጣጥ እና የክትትል ሥርአቶች ተግባራዊ ይሆናሉ።

2. የሥርዓተ ትምህርት ተጓዳኝ-እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት ከስርአተ ትምህርት ጋር የተያያዙ መስፈርቶች ላሏቸው ኮርሶች፣ የኮርስ መርሀ ግብሮች እንደአግባቡ የሥርዓተ ትምህርት ተጓዳኝ-እንቅስቃሴዎች የግዴታ መወሰድ እንዳለባቸው ለተማሪዎች መታወቅ አለበት።

   a) የኮርሱ መምህር በተቻለ መጠን ስለ ሥርዓተ ትምህርት ተጓዳኝ-እንቅስቃሴዎች ለተማሪዎች አስቀድሞ ማሳወቅ አለበ(ባ)ት።

b) የቅድሚያ ማሳወቂያ በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ ሊሰጥ በማይቻልበት ጊዜ የመማር-ማስተማር ክፍሉ የውጤት አሰጣጥ እንዴት መደረግ እንዳለበት እና እንደ ሁኔታው መተግበር ያለበትን ምክንያታዊ መመሪያ መስጠት አለበት።

3. አንድ ተማሪ በሥርዓተ ትምህርት ተጓዳኝ-እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሣተፍ ከተገመገመ(ች) እና ደረጃ ከተሰጠ በኋላ (ለምሳሌ፦ የሙዚቃ ባንድ፣ መዘምራን፣ ኦርኬስትራ፣ የቲያትር ወይም የዳንስ ልምምዶች ወይም ትርኢቶች) ላይ ለመሳተፍ ፍቃድ ሊከለከል አይችልም።

***ተዛማጅ ምንጮች፦*** MCPS *የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች*፣ MCPS *የተማሪ ስነምግባር ደንብ*

***የአፈጻጸሙ ታሪክ፦*** ማርች 23, 1979 የቀድሞው ደንብ ቁጥር 520-2 ጃኑዋሪ 1986 ተሻሽሏል።ጁን 8, 2020 ጉልህ ያልሆኑ ጭብጦችን ክለሳ ተደርጓል፤ ጁን 27, 2025 ተሻሽሏል፣ ከጁላይ 1, 2025 ጀምሮ ባሉት የይዘት መረጃዎች ላይ ቴክኒካዊ ዝመና ተደርጓል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜኘት መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ***</td><td>MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ ***</td></tr>
<tr><td>Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org